ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቁ. 005
ሐምሌ 2017 ዓ.ም



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

BRIDGE Research & Innovation-
Parliaments. Peace. Policy

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ::
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል


+251 911 86 12 34

+251 115 57 74 96

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.









# ማውጫ


በወሩ የተካሄደ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ ..... 1

የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት ..... 2

የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ..... 7

እንደራሴዎቹ የውክልና ስራ ..... 9

የፓርላማው ዲፕሎማሲ ..... 11

እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው ..... 14

ጉባኤው ..... 16

ሹመት ..... 18

የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ ..... 19

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በእረፍት እና የሥራ ጊዜ ማሻሻያ ዐዋጅ ቁጥር 263/1994 ዓ.ም. መሰረት፣ የእንደራሴዎቹ የእረፍት ጊዜ በየዓመቱ ከየካቲት 1 እስከ 30 እና ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ ዋዜማ ድረስ መሆኑ ተደንግጓል። ያም ሆኖ፣ ምክር ቤቱ ወደ እረፍትም ሳይገባ በወርኃ ሐምሌ የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹን ከውኗል። ከእነዚኽ ዋንኛ ኃላፊነቶቹ መካከልም፣ ሕግጋት ማውጣት፣ የሥራ አሥፈፃሚ ተቋማት ሪፖርቶችን ማድመጥ፣ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ የፌደራል ተቋማትን መጎብኘት እና የመራጭ ተመራጭ ውይይቶችን ማድረግ የወሩ የምክር ቤቱ አበይት ክንውኖች ነበሩ። ከዚኽ በተጨማሪም፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ይኽን መሰሎቹን ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹን በተሻለ መልኩ ይከውን ዘንድ አንድ ዓመታዊ ጉባኤም አካሂዷል። ይኽች የብሪፎ አምስተኛ ፣ እነዚኽን የምክር ቤቱን ዕትምም የሐምሌ ክራሞት ጨምሮ፣ በወሩ ያጸደቀውን የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅን ከብሪፎ አጭር ዳሰሳ ጋር አዳብላ እንዲህ ቀርባለች።

# በወሩ የተካሄደ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን

## 2ኛ አስቸኳይ ስብሰባ

ሐምሌ 9

### አጀንዳ

- የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅ ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ ዐዋጅ ን ማጽደቅ፤
- የፌዴራል የገቢ ግብር ዐዋጅ ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ ዐዋጅ ን ማጽደቅ፤
- የስታርታፕ ረቂቅ ዐዋጅን ማጽደቅ፤

[1] 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 1ኛ አስቸኳይ ጉባዔ የካቲት 11 ቀን 2017 ዓ.ም. የተደረገ ሲሆን፣ በዕለተ ቀኑም የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽንን የ 3 ዓመት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት አድምጧል።

# የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት

የተወካዮች ምክር ቤት፣ በጠቀስነው ሐምሌ ወር ሦስት ሕግጋትን ሲያጸድቅ፣ በወሩ ውስጥ ወደ ቋሚ ኮሚቴዎች የተመሩ ረቂቅ ዐዋጆች ግን አልነበሩትም። እንደራሴዎቹ በዚህ ወር ባጸደቋቸው ሦስቱ ዐዋጆች ዙሪያም አስረጂ መድረኮችን አከናውነዋል፡፡



የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ እውነቱ አለነ

## የጸደቁ ሕግጋት

ሐምሌ ዐሥር ላይ 2ኛ አስቸኳይ ስብሰባውን ያደረገው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ካጸደቃቸው ሕግጋት መካከል አንዱ **የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅን** ለማሻሻል የቀረበውን ረቂቅ ዐዋጅ ነበር። ማሻሻያ ዐዋጁን አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት እና የወሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት፣ በምክር ቤቱ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ እውነቱ አለነ፣ የማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁ በነባሩ ዐዋጅ ቁጥር 1162/2011 ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶችን በማረም በፖለቲካ ፓርቲዎች አሥተዳደር፣ በምርጫ እና በምርጫ ሥነ-ምግባር የባለድርሻ አካላት መብት እና ግዴታ ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ድንጋጌዎችን ያካተተ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ረቂቅ ዐዋጁ ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮዎችን በመውሰድ እና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ጥርጣሬ እና ሥጋትን በማስወገድ ጊዜ እና ወጪን ሊቆጠብ በሚችል እንዲኹም ዘመናዊ አሠራርን ለመተግበር የሚያግዝ መሆኑን ሰብሳቢው አያይዘው ማብራራታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። ማሻሻያው፣ ከዚኽ በፊት የታዩ እና ወደፊትም ሊከሰቱ ይችላሉ ተብሎ የሚገመቱ ተግዳሮቶችን በመቅረፍ የፖለቲካ ምኅዳሩን በማስፋት፣ ፍትሐዊ እና ተዓማኒነት ያለው የምርጫ ሂደት እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ሲናገሩ የተደመጡት እውነቱ አለነ፣ ከዚኽ ባለፈ ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን እና ወጣቶችን በምርጫ ለማሳተፍ ዕድል የሚፈጥር እና በምርጫ ሂደት የሚነሱ ቅሬታዎችን በተገቢው መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ነው ብለዋል ተብሏል።

የማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁን አስመልክቶ ከእንደራሴዎቹም በርካታ ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን፤ ከእነዚኽ መካከልም፣ በምርጫ ጣቢያ የነበረው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ለምን ቀረ? በሚል ለቀረበው ጥያቄ፣ በየምርጫ ጣቢያዎች ኮሚቴ ከመዋቀሩ ይልቅ በክልል ደረጃ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተዋቅሮ ለችግሩ በማዕከል ደረጃ ምላሽ እንዲሰጥበት ማድረግ እንደሚቻል ሰብሳቢው ምላሽ ያሉትን ሰጥተዋል። ሰብሳቢው ምላሻቸውን ሲቀጥሉ፣ የፓርቲ አባላት መዋጮ ክፍያን በተመለከተ ከ30 ወደ 20 በመቶ መቀነስ በመቻሉ፣ ምርጫ ቦርድ ፓርቲዎችን በገንዘብ ለመደገፍ ይህ እንደ ግዴታ አይታይም ብለዋል፤ ከዚኽ በተጨማሪም፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በራሳቸው ውስጠ ደንብ እና መመሪያ መሠረት መተግበር የሚችሉ መሆኑን እውነቱ ጠቁመዋል፡፡ በአገር ደረጃ አዳዲስ ክልሎች መመስረታቸው፣ አገራዊ ፓርቲ ለመመሥረት ከአኹን በፊት በአራት ክልሎች የድርጅት አባል ማፍራት አለባቸው የሚለው አኹን ላይ ወደ ስድስት ክልሎች እንዲያድግ መደረጉን ጨምረው መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

እንደራሴዎቹም፣ ይኽንኑ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ፣ ዐዋጅ ቁጥር 1394/2017 አድርገው በኹለት ተቃውሞ በአራት ድምጸ ተዐቅቦ በአብላጫ ድምጽ አፅድቀውታል። (በዚኽ ዐዋጅ እና ተያያዥ በሆነው የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ተቋማዊ ማሻሻያ ዙሪያ የብሪጅን አጠር ያለ ዳሰሳ በገጽ 19 ይመለከቷል)።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በዚያው ዕለት ያጸደቀው ኹለተኛው ዐዋጅ፣ ነባሩን **የገቢ ግብር ለማሻሻል የቀረበለትን ረቂቅ ዐዋጅ** ነበር። ረቂቅ ዐዋጁን አስመልክቶ ለእንደራሴዎቹ ማብራሪያ የሰጡት በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ የገቢ ግብር ዐዋጁ በሥራ ላይ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ በመሆኑ የንግዱን ውስብስብ ባህሪ ያማከለ ዘመናዊ የግብር አሰባሰብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ዐዋጁ እንዲሻሻል መወሰኑን ተናግረዋል። ማሻሻያው ከዲጂታል ኢኮኖሚው ጋር የተጣጣመ ዘመናዊ የግብር መሠረት እንዲኖር ለማድረግ እና ለግብር ማጭበርበር በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ለመቀየር የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ማካተቱን ሰብሳቢው መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል። ከዚኽ ባለፈም፣ የግብር መሠረትን በማስፋት፣ የመንግስት ገቢ አሰባሰብን በማሻሻል እና የግብር ፍትሐዊነትን በማረጋገጥ የመንግስትን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች በዐዋጁ መካተታቸውን ጨምረው የገለጹት ደሳለኝ፣ ማሻሻያው ምቹ እና ቀላል የግብር ሥርዓትን በመዘርጋት ለአገሪቷ የተሻለ ኢኮኖሚ ለመፍጠር የሚያስችል ነው ማለታቸው ተሰምቷል።

እንደራሴዎቹም፣ የገቢ ግብር ማሻሻያው የመንግስት ሠራተኛውን የኑሮ ኹኔታ ታሳቢ ያላደረገ ማሻሻያ በመሆኑ ምክር ቤቱ ማሻሻያውን በድጋሚ እንዲፈትሸው ሲጠይቁ ተደምጠዋል። ለዚኽ መሰሉ ጥያቄ ምላሽ የሰጡት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ፣ በማሻሻያው ላይ ከበርካታ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እንደተደረገበት እና እንደ ቋሚ ኮሚቴም ሰፊ ጊዜ ተወስዶበት የተዘጋጀ ማሻሻያ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል። በዚያው መድረክ ላይ የተገኙት የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. ኢዮብ ተካልኝ በበኩላቸው፣ ማሻሻያው ለረጅም ጊዜ ውይይት እንደተደረገበት እና የአገራት ልምድ እንደተወሰደበት ጠቅሰው፣ ማሻሻያው ዘመኑን የዋጀ ነው ሲሉ ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። ሚኒስትር ዴኤታው አክለውም፣ የመንግስት ሠራተኛውን የኑሮ ኹኔታ ለማሻሻል ከገቢ ግብር ማሻሻያ በተጨማሪ የመኖሪያ ቤት ጥናት እየተደረገ መሆኑን መናገራቸውን ዘገባው ያሳያል። ምክር ቤቱም የገቢ ግብር ማሻሻያ ዐዋጁን በአምስት ተቃውሞ በዐሥራ ኹለት ድምጸ ተዐቅቦ በአብላጫ ድምጽ አፅድቆታል፡፡

የኢትዮጵያ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በዚያው ሐምሌ 10 ቀን ያጸደቀው ሦስተኛው ዐዋጅ፣ ለወጣቶች እና ታዳጊዎች ከፍተኛ የሥራ ዕድል ይፈጥራል የተባለውን **የስታርታፕ ረቂቅ ዐዋጅን** ነበር። በምክር ቤቱ የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ የተደገፈ የስታርታፕ ውጤት በሂደት ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችን እና ኩባንያዎችን በማፍራት ለኢኮኖሚ ዕድገት እና ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ረቂቁን ባቀረቡበት ወቅት መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። ሰብሳቢው አክለውም፣ ስታርታፕ ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ አቅም በመጠቀም የኢኮኖሚ ዕድገት እና ልማትን ለማፋጠን ቁልፍ ሚና ያለው እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን የሚያስችል ነው ብለዋል ተብሏል። ከዚኽ ባለፈም፣ ስታርታፖችን እና የስትርታፕ ምኅዳር ገንቢዎች የሚያጋጥማቸውን የፋይናንስ አቅርቦት ተግዳሮቶች እና የፋይናንስ ስጋትን በዘላቂነት ለመቅረፍ የግራንት ፕሮግራም፣ የብድር ዋስትና ማዕቀፍ እና የፈንዶች ፈንድ መዋቅር ማደራጀት የሚያስችል ዐዋጅ እንደሆነም ሰብሳቢው መናገራቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል። እንደራሴዎቹም፣ ዐዋጁን ዐዋጅ ቁጥር 2320/2017 በማድረግ ዐዋጅ በሙሉ ድምጽ አፅድቀውታል።



በምክር ቤቱ የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ

## አስረጂ መድረኮች



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኃ ሐምሌ ያደረጋቸው የአስረጂ መድረኮች፣ በዚያው ወር ባጸደቃቸው ሦስቱ ዐዋጆች ዙሪያ ያካሄዳቸው ኹለት ኹለት መድረኮች ነበሩ። በቀዳሚነት የተካሄደው የአስረጂ መድረክ፣ ከጥቂት ዓመታት በፊት ጸድቆ በሥራ ላይ የነበረውን **የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅን ለማሻሻል የቀረበውን ረቂቅ ዐዋጅ** ነበር።

አስቀድሞ ሐምሌ 2 ላይ የተካሄደው ውይይት፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው፣ ከምክር ቤቱ የሕግ ክፍል እና ከምርጫ ቦርድ አመራሮች ጋር ያካሄደው ሰፊ የተባለ ውይይት ነበር። ምርጫ ቦርድ በ6ኛው ዙር አገራዊ ምርጫ የታየ ክፍተቶችን ለመሙላት እና ጥንካሬዎችን ለማስቀጠል ያደረገውን ጥረት ያደነቀው ቋሚ ኮሚቴው፣ በተለይም የፖለቲካ ፓርቲዎች በሂደት ‘ራሳቸውን እየቻሉ እንዲሄዱ ለማስቻል ከአባሎቻቸው 30 በመቶ መዋጮ እንዲሰበስቡ የሚያስገድደው ድንጋጌ የሚመሰገን ነው ማለቱን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። ኢትዮጵያ በልምምድ ላይ ያለ ዲሞክራሲ እንዳላት የጠቆመው ቋሚ ኮሚቴው፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች በኩል ለሚፈጠሩ ስህተቶች ከማሰረዝ ይልቅ ደረጃ በደረጃ እያረሙ እና እያስተማሩ መሄድ የፖለቲካ ምኅዳሩን እንደሚያሰፋ እና የፓርቲዎቹንም በጎ አስተዋጽኦ ከፍ እንደሚያደርግ አሳስቧል ተብሏል። አገር አቀፍ ፓርቲዎች ሲመሰረቱ ነዋሪነታቸው በሰባት ክልሎች የሆኑ አባላት እንዲኖራቸው የሚለው ሐሳብም፣ ፓርቲዎቹ አገራዊ ገጽታ እንዲላበሱ እንደሚያደርግ አመላክቷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ አውነቱ አለነ በበኩላቸው፣ ምርጫ ቦርድ ከዓለም ዓቀፍ ልምዶች በተጨማሪ የራሱን ተሞክሮ ተጠቅሞ ያቀረበው የማሻሻያ ዐዋጅ የሚደነቅ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል።

ከዚኽ ውይይት ኹለት ቀናት በኋላም፣ በዚኹ ዐዋጅ ዙሪያ ይኸው የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከባለድርሻ አካላት እና ከሲቪል ማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር ይፋዊ የሕዝብ የውይይት መድረክ አካሂዷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ እውነቱ አለነ፣ ረቂቁ ፓርቲዎች በሚያጠፉ ጊዜ ከመሰረዝ ይልቅ የተፈፀመውን ጥፋት እና ስህተት በሚመልስ ልክ እገዳ የሚጥል በመሆኑ ድጋፍ ሊሰጠው ይገባል ሲሉ በመድረኩ ላይ መናገራቸው ተሰምቷል። የውይይቱ ተሳታፊዎችም፣ በረቂቅ ዐዋጁ ላይ የተለያዩ ጥያቄዎችን ያነሱ ሲሆን፣ ቢካተቱ እንዲኹም ሊሻሻሉ ይገባል ያሏቸውን በርካታ ሐሳቦችንም አንስተዋል ተብሏል፡፡ ከተነሱት ሐሳቦች መካከልም፣ ምርጫው በዲጂታል መሆኑ የአገራችንን እድገት የሚያሳይ ቢሆንም ደህንነቱ ምን ያህል የተጠበቀ ነው?፣ አንድ የፓለቲካ ፓርቲ በምርጫ ወቅት ከመንግስት የሚሰጠውን ድጋፍ ለማግኘት ከአባላቱ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ቢያንስ 30 በመቶ መዋጮ መሰብሰብ አለበት የሚለው የተጋነነ ነውና ወደ 5 በመቶ ዝቅ ቢል?፣ የእጩዎች ብሔራዊ መታወቂያን አስገዳጅ ማድረግ የመራጮችን መብት ይጋፋልና ቢስተካከል የሚሉት ዋንኞቹ ነበሩ።

በዚያ የአስረጂ መድረክ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሜላትወርቅ ኀይሉ፣ 30 በመቶ የአባላት መዋጮ የሚለው ድንጋጌ፣ አባላቱ ለፓርቲያቸው ያላቸውን ቁርጠኝነት ከግምት ያስገባ እና ጠንካራ ፓርቲ ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት ያግዛል ሲሉ ምላሽ ያሉትን ሰጥተዋል፡፡ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ የኤሌክትሮኒክስ ምርጫ ሳይሆን ፓርቲዎችም ሆኑ የግል ተወዳዳሪዎች ‘ራሳቸውን የሚመዘግቡበት ሂደት መሆኑን ያነሱት ሜላትወርቅ፣ አካታችነትን በሚመለከትም ማየት እና መስማት የተሳናቸውን ወገኖች ያካተተ ነው ብለዋል፡፡ የፋይዳ ዲጅታል መታወቂያ አስገዳጅነት የተቀመጠው ለእጩዎች እንጂ ለመራጮች አይደለም ያሉት የቦርዱ ሰብሳቢ፣ የወጣቶችን ተሳትፎን አስመልክቶም ሲናገሩ፣ በመራጭነት ለመመዝገብ እድሜው 18 ዓመት፣ በእጩነት ለመቅረብ 21 ዓመት የሞላው የሚለውን ከምዝገባ ቀን ሳይሆን ከድምፅ መስጫው ቀን አኳያ ታሳቢ እንዲሆን መሻሻሉን ጠቁመዋል፡፡ ሰብሳቢው አክለውም፣ በማሻሻያ ረቂቁ የመንግስት ሠራተኞች ምርጫ በሚወዳደሩበት ጊዜ ደመወዝ እየተከፈላቸው በምርጫ ይወዳደራሉ የሚለው ድንጋጌ ከዚኽ በፊት ያልነበረ ነው ሲሉ ለመድረኩ ተሳታፊዎች ማብራራታቸው ተሰምቷል።

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኹለተኝነት ያካሄደው የአስረጂ መድረክ፣ ዘግየት ብሎ በዚያው ወር ያጸደቀውን **የገቢ ግብር ማሻሻያ ዐዋጅን** አስመልክቶ ነበር። የዜጎችን የኑሮ እና የግብር ጫና ለመቀነስ ያስችላል የተባለውን ይኽንኑ ረቂቅ አስመልክቶ፣ የፕላን በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና በምክር ቤቱ ሕግ ክፍል የቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ከገንዘብ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ጋር የአስረጂዎች ውይይት ተደርጓል፡፡

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. ኢዮብ ተካልኝ፣ ማሻሻያው የዜጎችን የኑሮ እና የገቢ ግብር ጫና ታሳቢ ያደረገ እና በአነስተኛ የንግድ ሥራ የተሰማሩ ዜጎችን የሚደግፍ መሆኑን አሰረድተዋል ተብሏል። የረቂቅ ዐዋጁ ዋነኛ አላማዎችም፣ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያለውን የግብር ጫና መቀነስ፣ የግብር መሰረትን ማስፋት እና ለአነስተኛ የንግድ እንቅስቃሴዎች ቀላል የግብር አከፋፈል ሥርዓት መዘርጋት መሆናቸውን ዴኤታው አብራርተዋል። መዋዕለ ንዋይን ለመደገፍ የሚደረግ የግብር ቅነሳ ወጥነት ያለው ለማድረግ እና የግብር ስወራ እና ማጭበርበርን ለመከላከል ያስችላል ያሉት ኢዮብ፣ ግብር ከፋዮች ከ30 ሺሕ ብር በላይ በጥሬ ገንዘብ ግብይት እንዳይፈፅሙ ረቂቅ ዐዋጁ ይከለክላል ብለዋል።

በዚኹ የግብር ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ፣ በምክር ቤቱ የፕላን በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይፋዊ የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ ነበር። በውይይት መድረኩ ላይ የተገኙት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ የዐዋጁ መሻሻል መንግስት ግብር በመሰብሰብ ከሕዝቡ የሚነሱ የተለያዩ የልማት ጥያቄዎችን ለመመለስ እንደሚረዳ ጠቁመዋል፡፡ ከግብር ከፋዩ ኅብረተሰብ ደግሞ ግብር በዝቷል ይቀነስ በሚል የሚቀርቡ ሐሳቦች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚታይ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየኹ በበኩላቸው፣ የሚወጡ ሕጎች የዜጎችን እና የመንግስትን ጥቅም የሚያስጠብቁ መሆናቸውን በደንብ ማየት ያስፈልጋል ከማለታቸው ባለፈ፣ የኑሮ እና የግብር ጫና ያለባቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ታሳቢ ያደረገ እና ከግብር ሥርዓት ጋር ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ያለመ ማሻሻያ ረቂቅ መሆኑንም መናገራቸውን መረጃው ይጠቁማል፡፡ በዚኹ የውይይት መድረክ ላይም፣ የተለያዩ ግልጽነት የሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች እና መካተት ወይም መሻሻል አለባቸው የሚሉ አስተያየቶች ተደምጠዋል፡፡ ከኑሮ ውድነቱ እና ከዋጋ ንረት አኳያ 35 በመቶ የሚለው የገቢ የግብር መጠን መቀነስ እንዳለበት እና 2ሺሕ የሚለው የገቢ ግብር መነሻው ከፍ ማለት እንዳለበት የሚሉት ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል ዋንኞቹ ነበሩ። በመድረኩ የተገኙት ሌላይኛው የገንዘብ ሚንስቴር ባለሥልጣን ፍቃዱ ሆረታ እና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ለእነዚኽ መሰሎቹ ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ መስጠታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወርኃ ሐምሌ ያከናወነው ሦስተኛው የአስረጂ መድረክ፣ በዚያው ሐምሌ ዐሥር በጸደቀው **በስታርታፕ ረቂቅ ዐዋጅ** ዙሪያ ያካሄደው ነበር። ለኢትዮጵያ ወጣቶች ከፍተኛ የሥራ ዕድል ይፈጥራል የተባለውን የስታርታፕ ረቂቅ ዐዋጅን አስመልክቶ፣ በምክር ቤቱ የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር የአስረጂ መድረክ አካሄዷል። በአስረጂ መድረኩ ላይ የተገኙት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ በአኹኑ ወቅት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 70 በመቶው የሚሆነው በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኝ አንስተው፣ ከዚኽ አንፃር ረቂቅ ዐዋጁ የተለያዩ የዕውቀት እና ተሰጥዖ ባለቤት የሆኑ ወጣቶችን ከፍተኛ የፋይናንስ አቅም ካላቸው አገራዊ እና ዓለም ዓቀፍ ባለሀብቶች እና ድርጅቶች ጋር በማስተሳሰር ከፍተኛ የሆነ ሀብት እንዲፈጥሩ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል። የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ዶ.ር. በለጠ ሞላ በበኩላቸው፣ የአገርን ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማጎልበት እና ለወጣቱ ከፍተኛ የሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ አዳዲስ የሀብት ምንጮችን መሞከር እንደሚገባ ገልጸዋል ተብሏል። ዐዋጁ ስታርታፕን ዒላማ ያደረገ ድጋፍን ለመስጠት የሚያስችል የተሳለጠ ሂደት እና ሥርዓት ለማስተዋወቅ፣ የስታርታፕ ምኅዳርን ለማሳደግ የተጀመሩ እንቅስቃሴዎችን አጠናክሮ ለመቀጠል፣ የግራንት ፕሮግራም፣ የብድር ዋስትና ማዕቀፍ እና የፈንዶች ፈንድ መዋቅርን ለማደራጀት ጠቃሚ እንደሆነም ሚኒስትሩ በዚያው መድረክ መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

በዚኹ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ በተዘጋጀ ሌላ ይፋዊ ሕዝባዊ መድረክ ላይ የተገኙት የዚኹ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ በውይይቱ ላይ ቁልፍ ሐሳቦች ተነስተዋል ማለታቸው ተዘግቧል። በውይይቱ መግቢያ ላይ የስታርታፕ ረቂቅ ዐዋጅ ዓላማ፣ ትርጉም፣ ስለተፈጻሚነት ወሰን እንዲኹም የኮሚቴው ስልጣን እና ተግባር፣ ለስታርታፕ የሚሆኑ ግራንድ ፈንድ እና ዋስትና ፈንድ ሐሳብ፣ ግዴታ እና ክልከላዎች በዝርዝር ቀርበው ውይይት እንደተደረገባቸውም ተዘግቧል። በውይይቱ ላይ ከተገኙ ተቋማት መካከልም ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲኹም በስታርታፕ ላይ ጥናት እና ምርምሮችን ሲሰሩ የነበሩ ግለሰቦችም ነበሩበት ተብሏል። የውይይቱ ተሳታፊዎች በረቂቅ ዐዋጁ ዙሪያ ካነሷቸው በርካታ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች መካከል፣ እንደግብርና ባሉ ብዙ መሻሻል በሚያስፈልጋቸው ዘርፎች ላይ በዋናነት ትኩረት ሰጥቶ መሰራት እንዳለበት፣ ከገቢ ግብር ጋር በተገናኘ የተጠቆሙት አቅጣጫዎች በድጋሚ ትኩረት እንዲደረግባቸው፣ የማበረታቻ ሂደቱ ከመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ማበረታቻ ጋር ትንሽ ስለሚጣረስ በድጋሚ ቢታይ የሚሉ እና ሌሎችም እንደሚገኙበት ለማወቅ ተችሏል።

# የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደራሴዎች፣ ከዋና ዋና ሥራዎቻቸው አንዱ የሆነው የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ሲሆን፤ በዚኽ ረገድም፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ሐምሌ ብቸኛው ሪፖርት አቅራቢ አሥፈጻሚ ተቋም የግብርና ሚኒስቴር ሲሆን፣ የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴም አንድን ተቋም ጎብኝቷል፡፡




የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር የተከበሩ ዶ.ር. ግርማ አመንቴ

## የተቋማት ሪፖርቶች

በወርኃ ሐምሌ፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የግብርና ሚኒስቴር በቅንጅት በ2017/18 ምርት ዘመን የግብርና ግብዓት አቅርቦት እና ስርጭት ላይ የተደረገ የክትትል እና ቁጥጥር ሪፖርትን የገመገመበት ኹነት ነበር።

በውይይቱም፣ የአፈር ማዳበሪያ፣ የምርጥ ዘር፣ የኬሚካል አቅርቦት እና ስርጭት ከምን ደረጃ ላይ እንዳለ፣ ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ በሜካናይዜሽን የታገዘ የግብርና ሥራ ተግባራዊነት አፈፃፀም ሪፖርት ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል ተብሏል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰለሞን ላሌ፣ የግብርና ግብዓት ወደ አርሶ አደሩ መድረሱን እና ወደ ሚፈለገው ግብ መቀየሩን ማረጋገጥ፣ በሂደቱ የተሰሩ መልካም አፈፃፀሞችን ማበረታታት፣ በታችኛው አካል የማይፈቱትን በግብርና ሚኒስቴር እና በከፍተኛ አመራሮች ቶሎ እንዲፈቱ በማስቻል ምርት እና ምርታማነት እንዲጨምር አስተዋፅኦ ማድረግ የተቋጣጣሪ ቡድኖቹ ዋንኛ አላማዎች መሆናቸውን መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። ከዚኽ በተጨማሪም ሰብሳቢው፣ ከበልግ ይልቅ የመኸር ወቅት በአገራችን በብዙ ክልሎች ከፍተኛ ምርት የሚመረትበት ወሳኝ ወቅት በመሆኑ፣ ቋሚ ኮሚቴው ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት 8 የቁጥጥር ቡድኖችን በማዋቀር በ11 ክልሎች ላይ እስከ አርሶ አደሩ ማሳ ድረስ በመውረድ የግብርና ግብዓት አቅርቦት እና ስርጭት ምን እንደሚመስል የቁጥጥር እና የክትትል ሥራ መሥራ ቱን ገልፀዋል፡፡ በአኹኑ ወቅት የግብርና ግብዓት አቅርቦቱ እና ስርጭቱ በጥሩ ኹኔታ ተካሂዷል ያሉት ሰብሳቢው፣ በተወሰኑ እጥረት በተስተዋለባቸው አካባቢዎች ላይ በቀጣይ ማስተካከያ በማድረግ እጥረቱን መፍታት ይገባል ብለዋል ተብሏል፡፡ ሰለሞን አክለውም፣ መንግስት ከ84 ቢልዮን ብር በላይ መድቦ ዘርፉን ማጠናከሩን፣ ነገር ግን የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ ጨምሯል በማለት አርሶ አደሩ ማዳበሪያ ወስዶ ምርት እና ምርታማነትን እንዳያሳድግ የሚያደርጉ ጉዳዮች ስለነበሩ ታች ድረስ በመውረድ አመርቂ ሥራ በመሰራቱ የግብርና ግብዓት ስርጭቱ ውጤታማ ሆኗል ብለዋል ተብሏል፡፡ የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር የተከበሩ ዶ.ር. ግርማ አመንቴ በበኩላቸው፣ ዳፕ ቅድሚያ እንዲገዛ መደረጉን ጠቀመው፣ በአቅርቦት እና በስርጭት በኩል በዚኽ ዓመት ከፍተኛ መሻሻሎች መኖራቸውን መግለፃቸው ተሰምቷል። አምና የገቡ 3 መርከብ ዩሪያ ማዳበሪያ እጃችን ላይ በመኖሩ የዩሪያ ግዥ ቢዘገይም በቅርቡም ተጨማሪ ዩሪያ ማዳበሪያ የጫኑ 5 መርከቦች ጅቡቲ ወደብ ይደርሳሉ ያሉት ግርማ፣ እንደ ግብርና ሚኒስቴር በዘንድሮው ዓመት ኹሉም ክልሎች የማስፈፀም አቅማቸው እያደገና እየተሻሻለ በመምጣቱ ክልሎች የሚያስፈልጋቸውን የግብዓት መጠን የመለየት፣ አቅማቸውን የመመጠንና የማወቅ ደረጃቸው ከፍ ማለቱን መገንዘባቸውን ገልፀዋል።

# የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ሐምሌ አንድ ተቋምን በሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ በኩል ጎብኝተዋል፡፡

## የተቋም ጉብኝት

የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወሩ ያደረገው ብቸኛው የተቋም ጉብኝት፣ **በአዲስ አበባ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ** ያደረገው ነበር። ሐምሌ 15 ዩኒቨርሲተውን የጎበኘው፣ በምክር ቤቱ የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ዩኒቨርሲቲው በሚያከናውናቸው የምርምር እና ሌሎች ተግባራት ፈር ቀዳጅ እና ወደ ራስገዝ ዩኒቨርሲቲነት ለመሸጋገር በዝግጅት ላይ ለሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ጥሩ ማሳያ መሆን እንዳለበት አሳስቧል ተብሏል። ቋሚ ኮሚቴው፣ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ ከሆነ ጀምሮ እየተገበረ ባሉት ሥራዎች ዙሪያ ያካሄደውን የመስክ ምልከታ አስመልክቶ የማጠቃለያ ግብረ-መልስ ሰጥቷል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ቤተልሔም ላቀው፣ መንግስት የአገሪቱን ልማት ለማፋጠን በዋነኛነት ተቋም ግንባታ ላይ አትኩሮ እየሰራ መሆኑን ጠቀመው፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ወደ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲነት መሸጋገርም አንዱ አካል መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል። ዩኒቨርሲቲዎች የተማረ የሰው ኃይል ከማፍራት ባሻገር የአገሪቱን እና የማኅበረሰቡን ችግር የሚፈቱ የጥናት እና ምርምር ውጤት መገኛ መሆን እንዳለባቸውም አሳስበዋል። ለዚኽም ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ እንዲሆን በዐዋጅ እና በፖሊሲ ጭምር በመደገፍ የራሱ የሆነ የአሥተዳደር፣ የምርምር፣ የፋይናንስ፣ የአካዳሚክ እና ሌሎች ተጠያቂነት ያለበት ነፃነት እንደተሰጠው ጨምረው ማስታወሳቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ.ር. ሳሙኤል ክፍሌ እና የሥራ ባልደረቦቻቸው፣ የአዲስ አበባ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ በዋነኛነት ለሚያከናውናቸው የጥናት እና ምርምር ሥራዎች የበጀት እጥረት ያለበት መሆኑን ጠቀመው፣ ቋሚ ኮሚቴው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር መፍትሔ እንዲፈልግላቸውም ጠይቀዋል ተብሏል።

# የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ

በዚኽች የብሪጅ አራተኛ ዕትም ሽፋን የሰጠነው ሐምሌ ወር፣ ለእንደራሴዎቹ የመራጭ ተመራጭ መድረኮችን መከወኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚኽ አኳያም ጥቂት የመራጭ ተመራጭ መድረኮችን በማከናወን ወሩን አጠናቀዋል፡፡





በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሐረሪ ክልል ተወካዮች
የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ እና ወ/ሮ ሰሚራ ዩሱፍ በክልሉ ከሶፊ ወረዳ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት፤

የወሩ ቀዳሚ የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ፣ **በሐረሪ ክልል** ከሚገኙ ወረዳዎች ከተወጣጡ የማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር ያደረጉት ውይይት ነበር። በውይይቱ ላይ የተገኙት የምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ፣ ባለፉት ስድስት ወራት በኅብረተሰቡ የተነሱ ጥያቄዎች በፌደራል ደረጃ ምላሽ እንዲሰጥባቸው ጥረት እየተደረገ መቆየቱን ገልጸዋል ተብሏል። በክልሉ የሚስተዋለውን የመጠጥ ውኃ ችግር ለመቅረፍ የተጀመሩ ሥራዎች መኖራቸውን በዚያው ውይይት ላይ ያነሱት ሰብሳቢው፣ ምሥራቅ ሐረርጌን ከኮምቦልቻ ጋር የሚያገናኘው መንገድ ወደ ሥራ እየተመለሰ መሆኑን እና በቀጣይም በፍጥነት ተጠናቅቆ ወደ ሥራ እንዲገባ ክትትል እንደሚያደርጉ ተናግረዋል። ሌላይኛዋ እንደራሴ ክብርት ሰሚራ ዩሱፍ በበኩላቸው፣ የሕዝቡን ጥያቄዎች ለመስማት እና ምላሽ ለመስጠት በየስድስት ወሩ የተለያዩ ግምገማዎችን እያካሄዱ መሆኑን እና በፌዴራል መንግስት ዐዋጆች መሰረት ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀራርበው እየሰሩ መሆኑን መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል።

ከወረዳዎቹ የተወጣጡ የኅብረተሰብ ተወካዮችም ለቋሚ ኮሚቴ አባላቱ የተለያዩ አስተያየቶችን እና ጥያቄዎችን አቅርበዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢው በሰጡት ምላሽም፣ ከማኅበረሰቡ የተነሱ ጥያቄዎች በክልል ደረጃ የሚፈቱ ከመሆናቸው ባለፈ፣ በፌደራል መንግስት በኩል መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎችም ምላሽ እንዲያገኙ ክትትል የሚደረግ መሆኑን መግለፃቸውን ለመረዳት ተችሏል።

የወሩ ኹለተኛው የውክልና ሥራ የተከወነው፣ ወደ **አማራ ክልሏ ደሴ** ከተማ በሄዱት የተከበሩ ዶ.ር. ማኅተመ ኃይሌ አማካኝነት ነበር። በዚያ የውክልና ሥራ ወቅትም፣ ጥራቱን የጠበቀ የበለፀገ ዱቄት በማምረት ረገድ እጥረት እየታየ መሆኑ ተገልፆል ተብሏል፡፡ ለዚኽም ዋነኛው ምክንያት የነርብ ዘንግ አፈጣጠር የጤና ችግር ለመከላከል የሚጠቅም አስገዳጅ የዱቄት ማበልፀግ ሥራ፣ በከተማይቱ በሚገኙ የዱቄት ፋብሪካዎች በኩል የማይካሄድ በመሆኑ ነው መባሉም ተዘግቧል፡፡



የተከበሩ ዶ.ር. ማኅተመ ኃይሌ፣ በደሴ ከተማ የሚገኘውን የዱቄት ፋብሪካ በመጎብኘት ላይ፤

ዶ.ር. ማኅተመ፣ ከከተማዋ ጤና መምሪያ የምግብ እና ምግብ ነክ ቁጥጥር የንግድ መምሪያ፣ በኢትዮጵያ ምግብ መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ እንዲኹም በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሰሜን ምሥራቅ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ጋር ጉዳዩን አስመልክቶ በጋራ መወያየታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይሳያል። በተደረገው የጋራ ውይይትም፣ ፋብሪካዎቹ በቅንጅት በመሥራት ጥራቱን የጠበቀ የበለፀገ ዱቄት በማምረት ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ፣ ማኅበረሰቡ የበለፀጉ ዱቄት እና ዘይቶችን በገበያ ላይ ገዝቶ እንዲጠቀም ግንዛቤ የመፍጠር እና በዱቄት እና ዘይት ምርቶቹ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር በማድረግ የነርብ ዘንግ የአፈጣጠር ችግርን የመከላከል ሥራ በመሥራት የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል ተብሏል።

# ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ሐምሌ ከአምስት ያላነሱ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎችን አከናውነዋል። እንደራሴዎቹ፣ ከናይሮቢ እስከ ጄኔቫ፣ ከደቡብ አፍሪካ እስከ አዲስ አበባ ድረስ በተካሄዱ የተለያዩ ፓርላማ ተኮር ጉባኤዎች ላይ ሲሳተፉ መሰንበታቸውን ከምክር ቤቱ ያሰባሰበናቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ።




የፓን አፍሪካ ፓርላማ 5ኛ መደበኛ ጉባኤ የተገኙት
የምክር ቤቱ ምክትል አፈ-ጉባኤ ክብርት ሎሚ በዶ፣ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የመንግሥት ረዳት ተጠሪ የሆኑት ክብርት መሰረት ሀይሌ፣ የተከበሩ ዶ.ር. አሸብር ወልደጎርጊስ፣ እና የተከበሩ ዶ.ር. አወቀ አምዛዬ

በወሩ የተካሄደው ቀዳሚው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ ሴት እንደራሴዎቹ እና ከግብርና ሚኒስቴር የተወጣጡ ባለሙያዎች በኬንያው መድረክ የተሳተፉበት ነበር። ለአምስት ቀናት ናይሮቢ ውስጥ በተዘጋጀው፣ በኢጋድ አባል አገራት መካከል **"በሥርዓተ-ጾታ፣ በመሬት እና በአየር ንብረት"** ዙሪያ በተካሄደው የጋራ የምክክር መድረክ የተሳተፉት እነኝ የልዑካን ቡድኑ አባላት፣ የአገራቸውን ተሞክሮ ከአባል አገራቱ ለተወጣጡት አቻዎቻቸው አቅርበዋል ተብሏል።

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ኹለተኛው የወሩ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ የተከወነው፣ በደቡብ አፍሪካ ሚዲራንድ ከተማ በተካሄደው **6ኛ የፓን አፍሪካ ፓርላማ 5ኛ መደበኛ ጉባኤ** ላይ በመሳተፍ ነበር። በጉባኤው ላይ፣ የምክር ቤቱ ምክትል አፈ-ጉባኤ ክብርት ሎሚ በዶ የመሩት የምክር ቤቱ የፓን አፍሪካ ቡድን መሳተፉ ሲሰማ፣ ጉባኤው ስለ አፍሪካ ዲሞክራሲ እና መልካም አሥተዳደር፣ ስለ አህጉሩ ሰላም እና ፀጥታ፣ ስለ ሰብዓዊ መብቶች አያያዝ፣ ስለ አህጉሩ የሰብዓዊ መብት ፍርድ ቤት፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ እየተወሰዱ ስላሉ የመፍትሔ እርምጃዎች እና መስል ተያያዥ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መክሯል ተብሏል። የሰው ሰራሽ አስተውሎትን በተመለከተ በጉባኤው የቀረበውን ጹሑፍ ተንተርሰው አስተያይት የሰጡት ሎሚ፣ ኢትዮጵያ በሰው ሰራሽ አስተውሎት ላይ ለ5 ሚሊዮን ኮደርስ ሥልጠና ከመስጠት ጀምሮ፣ በርካታ ውጤታማ ተግባራትን እያከናወነች መሆኑን አስረድተዋል ተብሏል። ሰው ሰራሽ አስተውሎት አኹን ያለንበት ዓለም እውነታ በመሆኑ አፍሪካም በዚህ ዘርፍ ወደ ኋላ እንዳትቀር ጠንክራ መሥራት እንዳለባት መናገራቸው የተሰማው ምክትል አፈ-ጉባኤዋ፣ ይህም ስኬታማ እንዲሆን ኢትዮጵያ ለዘርፉ ዕድገት ጉልህ አስተዋፅዖ እያበረከተች መሆኗን ተናግረዋል ተብሏል።

የአፍሪካ ሕብረት፣ የዘንድሮው 2025 (እ.አ.አ.) "የማካካሻ ዓመት" እንዲሆን በወሰነው መሰረት፣ "ፍትሕ ለአፍሪካ እና የአፍሪካ ዝርያ ላላቸው ሰዎች በማካካሻ" በሚል ዋና ጭብጥ ላይ አትኩሮ በተወያየበት ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያውያኑ እንደራሴዎች መገኘት፣ ሌላይኛው የወሩ ፓርላመንታዊ የዲፕሎማሲ ግብር ነበር። ጉባኤው የባሪያ ንግድ፣ የቅኝ ግዛት እና የዘር መድልኦ፣ በአፍሪካ እና የአፍሪካ ዝሪያ ባላቸው ሰዎች ላይ ላደረሱት ኢ-ፍትሐዊነት እና ታሪካዊ በደል ተገቢ ዕውቅና እንዲሰጥ፣ ሕጋዊ ተጠያቂነት እንዲኖር፣ ከባሪያ ንግድና ቅኝ ግዛት በፊት ወደነበረው የቀድሞ ሥርዓት እና ደህንነት በመመለስ ዕርቅ እንዲፈጠር፣ እንዲኹም ኹሉንም ባካተተ፣ በጠንካራ ማኅበራዊ ትስስር ላይ በመመስረት ወደ ዘላቂ ዕድገት እና ብልፅግና ሽግግር እንዲደረግ በሚያስችሉ ጭብጦች ላይ የመከረ ነበር።

በጉባኤው ላይ የተገኙት የተከበሩ ዶ.ር. አወቀ አምዛዬ፣ የግጭት መከላከል ቅድመ ማስጠንቀቂያ የአቻ ግምገማን አስመልክቶ በተነሳው ጉዳይ፣ ኢትዮጵያ ገንብታ በማጠናቀቅ ላይ ባለችው ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ሳቢያ ግብፅ ከኢትዮጵያ ጋር የገባችበት ውዝግብ ወደ ግጭት ሊያመራ ይችላል በሚል በአንድ ጽሑፍ አቅራቢ የተነሳው ሐሳብ የተሳሳተ በመሆኑ መታረም እንዳለበት አስገንዝበዋል ተብሏል። ኢትዮጵያ እና ግብፅ ድንበር እንደማይጋሩ የጠቀሱት አወቀ፣ በዚህም ምክንያት በኹለቱ አገራት መካከል ምንም ዓይነት የድንበር ግጭት እንደሌለ እና ግድቡም የግጭት ምንጭ ሊሆን እንደማይችል አበክረው ገልጸዋል ተብሏል። ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት፣ ኢትዮጵያን አግልሎ የአባይን ውኃ የመጠቀም ሙሉ መብት ግብፅ እንድትጎናፀፍ የሚያደርገው በብሪታንያ፣ ግብፅ እና ሱዳን መካከል የተደረጉ ስምምነቶች ናቸው ሲሉ የተደመጡት ዶ.ር. አወቀ፣ እነኚህ ስምምነቶች ጊዜ ያለፈባቸው የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነቶች በመሆናቸው፣ የአፍሪካ ህብረት እና የፓን አፍሪካ ፓርላማ እነኚህ የቅኝ ግዛት ስምምነቶች ሙሉ በሙሉ እንዲሰረዙ ብርቱ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

በጉባኤው ላይ ውይይት ከተደረገባቸው ርዕሰ ጉዳዮች መካከል ሌላይኛው፣ የአየር ንብረት ለውጥን አስመልክቶ አፍሪካ ያለችበትን አኹናዊ ኹኔታ ላይ ያጠነጠነ ነበር። በዚኽኛው የውይይት መድረክ ላይ የተገኙት በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ የሆኑት ክብርት መሰረት ኃይሌ፣ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እያከናወነች ያለችውን ተግባር፣ "ኢትዮጵያ ለዓለም እየተከለች ነው" በሚል ዋና ሐሳብ ላይ ያጠነጠኑ ሰፊ ሐሳቦችን በማንሳት አብራርተዋል ተብሏል። በዚህም መሰረት የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖ ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ጭምር ሥጋት እንደሆነ የጠቀሱት የመንግስት ተጠሪዋ፣ ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት በጠንካራ መሪዋ ግንባር ቀደም መሪነት እና ቁርጠኝነት እንዲኹም በኅብረተሰቡ ጠንካራ ተሳትፎ ውጤት እያስመዘገበች መሆኗን አብራርተዋል።

**ኢትዮጵያ እና ጣሊያን**፣ በተለያዩ ዘርፎች በትብብር ለመሥራት የተስማሙበት ኹነት ደግሞ፣ የወሩ ሌላይኛው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ክንውን ነበር። በጣሊያን ፓርላማ ምክትል ፕሬዝዳንት የተከበሩ ሊያ ኳርትፔሌ ፕሮኮፒያ የተመራው የልዑካን ቡድን፣ ከኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፍተኛ አመራሮች ጋር ኢትዮጵያ እና ጣሊያን በትብብር በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ላይ መምከሩ ተሰምቷል።



**በጣሊያን ፓርላማ ምክትል ፕሬዝዳንት የተከበሩ ሊያ ኳርትፔሌ ፕሮኮፒያ የተመራው የልኡካን ቡድን፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ተስፋዬ በልጂጌ እና ከሌሎች ምክር ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች ጋር በውይይት ላይ**

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚንስትር የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጂጌ፣ ጣሊያን እና ኢትዮጵያ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ መልካም ግንኙነት እንዳላቸው ጠቅሰው፣ ጣሊያን የኢትዮጵያ ቁልፍ የልማት አጋር መሆኗን እና በመሠረተ ልማት ዝርጋታ የምታደርገውን ጠንካራ ተሳትፎ አድንቀዋል ተብሏል። ኢትዮጵያ በአገር ውስጥም ሆነ በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም ይረጋገጥ ዘንድ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላት ያነሱት ተጠሪው፣ በኢትዮጵያ በአንዳንድ አከባቢዎች የሚስተዋለው ግጭት በአገር አቀፍ የምክክር ኮሚሽን እና በሽግግር ፍትሕ በኩል ዘላቂ እልባት ያገኝ ዘንድ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን እና ተስፋ ሰጪ ምልክቶች ስለመታየታቸውም ገልጸዋል ተብሏል፡፡ ኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣ የሕዝብ ቁጥር እና የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች በመሆኑ እያቀረበች ያለው የባሕር በር ጥያቄ በድርድር እና በዓለም ዓቀፍ ሕጎች ምላሽ ያገኝ ዘንድ ጣሊያንን ጨምሮ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት ሚናቸውን እንዲወጡም የመንግስት ተጠሪው ማስገንዘባቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። የጣሊያን ፓርላማ ምክትል ፕሬዝዳንት የተከበሩ ሊያ ኳርትፔሌ ፕሮኮፒያ በበኩላቸው፣ አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ኹለንተናዊ ትብብር በማስፋት በመሰረተ ልማት ዘርጋታ እና በተለያዩ ፕሮጀክቶች ግንባታ በትብብር ለመሥራት ቁርጠኛ መሆኗን ተናግረዋል ተብሏል። ኢትዮጵያ እያቀረበች ያለችው የባሕር በር ጥያቄ ተቀባይነት እንዳለው የጠቀሱት ኳርትፔሌ፣ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል ያለው ውጥረት ሰላማዊ እልባት ያገኝ ዘንድ ጣሊያን የበኩሏን ሚና እንደምትወጣም ገልጸዋል ተብሏል፡፡

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ የተሳተፉበት እና የፓርላማ አፈ-ጉባኤዎች የሚሰባሰቡበት አንድ ዓለም ዓቀፍ ጉባኤም በዚኹ ሐምሌ ወር ውስጥ ተካሂዶ ነበር። የፓርላመንቶችን ትብብርን እና የባለ ብዙ ወገንተኝነትን በማጠናከር ዙሪያ በ'የአምስት ዓመቱ በሚካሄደው በዚኽ **የኢንተር ፓርላማ ኅብረት ስድስተኛው ጉባኤ**፣ "ኹከት ውስጥ ላለ ዓለም የፓርላማ ትብብር እና የባለብዙ ግንኙነት ለሰላም፣ ፍትህ እና ብልጽግና ለኹሉም" በሚል ጭብጥ ዙሪያ ሰፊ ውይይት አካሂዷል። ከጉባዔው ጎን ለጎንም አፈ-ጉባኤው ከአውሮፓ ፓርላማ ምክትል ፕሬዝዳንት ካታሪና ባርሌይ ጋር ተገናኝተው በኢትዮጵያ እና በአውሮፓ ኅብረት ትብብር ዙሪያ መወያየታቸውን ከምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የወጣው መረጃ ያሳያል። በውይይቱም በኢትዮጵያ እና በኅብረቱ መካከል ለረጅም ጊዜ የዘለቀውን የፓርላማ ግንኙነት እና ለወደፊቱም ትብብሩን በሚያጠናክሩባቸው መንገዶች ላይ አፅንኦት ሰጥተው ተነጋግረዋል ተብሏል። በውይይቱ ከተነሱት ነጥቦች መካከልም መሠረተ ልማት፣ ዘላቂ ግብርና፣ ጤና፣ ትምህርት፣ የኃይል አቅርቦት እና ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን በዋነኛነት እንደሚገኙበት ታውቋል፡፡




የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ ከሐምሌ 23 - 26 ቀን 2017 ዓ.ም.
ድረስ፣ በስዊዘርላንድ ጄኔቫ በተካሄደው የኢንተር ፓርላማ ኅብረት (IPU)
ስድስተኛው የፓርላማ የአፈ-ጉባኤዎች ጉባኤ ላይ በተገኙበት ወቅት፤

የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ የተነሳበት አንድ ዓለም ዓቀፍ ጉባኤ ላይ፣ እንደራሴዎቹ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል የተሳተፉበት ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲም አንዱ የወርኃ ሐምሌ ክንውን ነበር። በዚኽ ሐምሌ 28 ቀን በቱርክሜኒስታን በተዘጋጀው ሦስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ባሕር በር የሌላቸው ታዳጊ አገራት ጉባኤ አካል በሆነው የፓርላማ አባላት ፎረም ላይ የተሳተፉት የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ፣ በቅድመ ጉባዔው በተካሄደ የፓናል ውይይት ላይ "የባሕር በር መዳረሻ የሌላቸው ታዳጊ አገራትን ተጠቃሚ የሚያደርግ የንግድ ሥርዓት ማቋቋም እና ማጠናከር" በሚል ርዕስ ጹሑፍ ማቅረባቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቁሟል። ኢትዮጵያ የባሕር በር መዳረሻ የሌላት አገር በመሆኗ የገጠሟትን ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶችን በጹሑፋቸው ያነሱት ዶ.ር. ፈትሂ፣ በዋናነት ከፍተኛ የሎጂስቲክስ ወጪዎች፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ ያልሆኑ የወደብ አገልግሎት እና ያልተሟሉ መሠረተ ልማቶች፣ የባሕር ላይ የደህንነት ስጋቶች እና በዓለም ዓቀፍ የእሴት ሰንሰለቶች ውስጥ የተገደበ ተሳትፎ ዋንኛ ተግዳሮቶች መሆናቸውን አብራርተዋል ተብሏል። ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እንደምትገኝ የጠቀሱት ሰብሳቢው፣ ነገር ግን አገሪቱ በዓለም ዓቀፉ የንግድ ሥርዓት ውስጥ ፍትሓዊ እና አካታች በሆነ መንገድ ለመሳተፍ አማራጭ የባሕር በር መዳረሻዎችን የግድ ማግኘት እንዳለባት በአጽንዖት መግለፃቸው ተሰምቷል። ዶ.ር. ፈትሂ አክለውም፣ ኢትዮጵያ ላለፉት ሦስት ዐሥርታት እና ከዚያ በላይ የባሕር በር መዳረሻ ሳይኖራት መቆየቷ በርካታ እና ዘርፈ ብዙ ችግሮች እንዲገጥማት ምክንያት ከመሆኑ ባለፈ፣ ወደ ኹለንተናዊ ዕድገት እና ብልጽግና በምታደርገው ጉዞ ላይ ትልቅ እንቅፋት መፍጠሩን ጨምረው ገልፀዋል ተብሏል።

# እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ ወርኃ ሐምሌን ያሳለፉት፣ ከላይ በዳሰስናቸው ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቻቸውን በመወጣት ብቻም ሳይሆን፣ በተለይም የሴት እንደራሴዎቻቸውን ስብስብ አልያም ኮከስ ዕቅድ እና የዚኽን ዓመት ክንውን በመገምገም፣ ለአባላቱ ሥልጠና በመስጠት እና ለቀጣዩ ዓመት ከፊል ዝግጅቶችን በማድረግ ነበር። ከላይ ከተጠቀሱት ክንውኖች ውስጥ ብሪጅ መድረኮችን እንደሚከተለው በአጭሩ ዳሰቸዋለች።

## የፓርላማ ተመራጭ ሴቶች ኮከስ የ2017 በጀት የዕቅድ አፈፃፀም



የምክር ቤቱ ምክትል አፈ ጉባኤ ክብርት ሎሚ በዶ በሴቶች ኮከስ ጉባኤ ላይ የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ

ምክር ቤቱ የሴቶች ኮከስ የ2017 በጀት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እና የቀጣይ ዓመት መሪ ዕቅድን እና ለኮከስ አባላት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በሚሰጡ የአቅም ግንባታ ሥልጠና አስመልክቶ፣ ለኮኮስ ሥራ አሥፈፃሚ እና አባላት በተሳተፉበት መድረክ ላይ ክብርት ሎሚ በዶ የመክፈቻ ንግግር ማድረጋቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። ምክትል አፈ ጉባኤዋ እንደገለፁት፣ እንደ አገርም ሆነ እንደ ምክር ቤት የሴቶች ውሳኔ ሰጭነት እና ተሳትፎ እያደገ የመጣ መሆኑን ጠቁመው፣ ሴቶችን በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ኮከሱ ሚናውን በይበልጥ መወጣት እንዳለበት አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡ የምክር ቤቱ የሴቶች ኮከስ ተልዕኮውን ከመወጣት አንፃር በበጀት ዓመቱ በርካታ ተግባራት ማከናወኑን የጠቀሱት ሎሚ፣ በቀጣይም የተመራጭ ሴቶች ኮከስ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት እና ልምድ እና ተሞክሮዎችን በማስፋት አገራዊ ኃላፊነትን መወጣት እንደሚገባም አሳስበዋል ተብሏል።

ከዚኹ የሴት እንደራሴዎች መረጃ ጋር በተያያዘ፣ የምክር ቤቱ የሴቶች ኮከስ የ2017 በጀት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት እና የቀጣይ ዓመት መሪ ዕቅድ ማጠቃለያ ውይይት መካሄዱ ተሰምቷል። በዚኽ ማጠቃለያ መድረክ ላይ የተገኙት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ሎሚ በዶ፣ የሴቶችን በኹሉም ዘርፎች ተጠቃሚ ለማደረግ ኮከሱ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንዳለበት አስገንዝበዋል ተብሏል። ከዚኹ ጋር በተገናኘ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ ክብርት መሠረት ኃይሌ፣ የምክር ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች ለኮከሱ መጠናከር ጉልህ አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን አስታውሰው፤ በሕፃናት እና ሴቶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጫና እና ጥቃት በዘላቂነት መፍታት ስለሚገባ የተመራጭ ሴቶች ኮከስ እና የምክር ቤት አባላት ወደ የምርጫ ክልል ሲሄዱ ከክልል ምክር ቤቶች እና በተዋረድ ካሉ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡ የፓርላማ ተመራጭ ሴቶች ኮከስ ምክትል ሰብሳቢዋ ክብርት አለሚቱ አበበ በበኩላቸው፣ ለሴት የምክር ቤት አባላት የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎች አበረታች ውጤት ማምጣታቸውን አስረድተው፣ በቀጣይም የአቅም ግንባታ ሥልጠናው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል፡ ፡ የምክር ቤት የኮከስ አባላት በበኩላቸው፣ በሕፃናት፣ ሴቶች እና በአካል ጉዳተኞች እየደረሰ ያለውን ጥቃት በጋራ መከላከል እንደሚገባ ገልጸዋል ተብሏል።



## የምክር ቤቱ የሴቶች ኮከስ የ2017 በጀት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት እና የቀጣይ ዓመት መሪ ዕቅድ የማጠቃለያ ውይይት፤

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በሴት አባላቱ ስብስብ ወይም ኮከስ ዙሪያ ብቻም ሳይሆን፣ ለእኒኹ ሴት እንደራሴዎቹ ሥልጠና በመስጠት ወሩን አገባዷል። እንደ ምክር ቤቱ መረጃ ከሆነም፣ “ከግጭት ወደ ሠላማዊ አውድ መሸጋገር” እና “የአመራር ለውጥ እና የተሳለጠ ተግባቦት” በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሥልጠናዎቹ ተሰጥተው ሰፊ ውይይት እንደተደረገባቸው ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል። በጉዳዩ ላይ የተናገሩት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ሎሚ በዶ፣ በሥልጠና የሚገኙ ዕውቀቶች እና ክህሎቶች ለተቋማት እና ለአገር ግንባታ ሚናቸው ከፍተኛ በመሆኑ ወደ ተግባር ቀይሮ ሥራ ላይ ማዋል እንደሚገባ አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡ የኮከሱ አባላት ለውክልና ሥራ ሲሄዱ በሥልጠና ያገኙትን ዕውቀት እና ክህሎት ተጠቅመው በየአካባቢው ያለውን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴን በማስፋት ኅብረተሰቡ እንዲተገብረው ማስገንዘብ እና ማስረጽ እንደሚገባ በዚያው መድረክ ላይ የተናገሩት ደግሞ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ ክብርት መሠረት ኃይሌ ነበሩ፡፡ የኮከሱ አባላት በበኩላቸው፣ የተሰጠው ሥልጠና አስተማሪ እና ለቀጣይ ሥራዎቻቸው አቅም የሚፈጥር መሆኑን ጠቁመው፣ በኹሉም አካባቢ ያሉ አገር በቀል የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም ለሠላም የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡ በግጭት ተጎጂዎች የሚሆኑት ሕፃናት እና ሴቶች እንዲኹም አረጋውያን በመሆናቸው በአገር ደረጃ ሠላምን ለማጽናት የሴቶች ሚና ከፍ ያለ መሆኑን ገልፀው፣ የኹሉም ዜጎች ትብብር እና ተሳትፎ መኖር እንዳለበት የኮከሱ አባላት አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡

## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃጸም



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት
የአስተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊና የዋና ጸሐፊ ተወካይ አቶ ከረዩ ባናታ



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት
የሙያዊ ድጋፍ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊ የሆኑት ዶ.ር. ንጉሴ መሸሻ

የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃጸም ሪፓርትን እና የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድን ከሠራተኞች ጋር የገመገመበት መድረክ ደግሞ፣ ሌላይኛው እንደራሴዎቹ ስለ ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው የከወኑት ተግባር ነበር። የጽሕፈት ቤቱ የአሥተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊ ከረዩ ባናታ፣ ጽሕፈት ቤቱ በ2017 በጀት ዓመት ሲጠበቅ የነበረውን የሠራተኞች ማሻሻያ ጨምሮ በርካታ ውጤታማ አሥተዳደራዊ እና ሙያዊ አገልግሎቶች መስጠታቸውን ገልፀዋል። ጽሕፈት ቤቱ በቀጣይ በጀት ዓመትም የተሻለ አፈፃፀም ለማስመዝገብ ተገቢውን ዝግጅት እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል ተብሏል። የጽሕፈት ቤቱ የሙያ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊ ዶ.ር ንጉሤ መሸሻ በበኩላቸው፣ በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ውጤታማ ተግባራት ስኬታማ እንዲሆኑ የሠራተኞች እና የአመራሩ ሚና ከፍተኛ እንደነበር አስታውሰዋል። በቀጣይም የጽሕፈት ቤቱ ሥራዎች ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ በጥናት እና ምርምሮች የማጠናከር እና የምክር ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴዎችን ለሕዝቡ ተደራሽ ለማድረግ የፓርላማ ቴሌቪዥንን በሙሉ ስርጭት ለማስጀመር እየተሰራ መሆኑን ማስረዳታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቁሟል።

# ጉባኤው

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ ዓመቱን ሊያጠናቀቁ በቀራቸው አንድ ወር ውስጥ ያካሄዱት ሊጠቀስ የሚችለው ኹነት፣ "ፓርላማዊ ተግባራትን ማጠናከር ለአካታች አስተዳደር፣ ለአገር በቀል ዕውቀት እና ለዘላቂ ልማት!" በሚል መሪ ቃል፣ የተካሄደው አምስተኛው ዓመታዊ የፓርላማ ጥናት እና ምርምር ጉባኤ ነበር። የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ያዘጋጀው ይኽ ጉባኤ፣ በአድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ሐምሌ ሦስት እና አራት ለኹለት ቀናት መካሄዱን የጉባኤው መረጃ ያሳያል። ይኽች የብሪጅ ዕትምም፣ በጉባኤው ከቀረቡት ፓርላማ ተኮር የጥናት ጹሑፎች መካከል ዋንኞቹን ነጥቦች አጠር አድርጋ ታቀርባለች።



ጥናት አቅራቢዎች በከፊል

በዚያ የፓርላማ ጥናታዊ መድረክ ላይ፣ ለኢትዮጵያ የፓርላማ ዴሞክራሲ ሥርዓት ትግበራ መሻሻል የፓርላማ ተግባራትን ማጠናከር፣ የሕግ የበላይነት፣ አካታች አሥተዳደር እና አገረ መንግሥት ግንባታ ላይ ያተኮሩ የተለያዩ ጥናታዊ ጹሑፎች በተመራማሪዎች ሲቀርቡ፣ በኢትዮጵያ የፓርላማ ዴሞክራሲ ሥርዓት ትግበራ መሻሻል ላይ ሰፊ ውይይቶች መካሄዳቸውን መረጃው ይጠቁማል። እንደ መረጃው ከሆነ፣ በዘንድሮው ዓመታዊ የፓርላማ ጥናታዊ ጉባኤ ላይ፣ 167 ጥናታዊ ጹሑፎች ለውድድር ቀርበው ዐሥራ ኹለቱ ተመርጠው ቀርበዋል ተብሏል።

በአምስተኛው ጉባኤ መክፈቻ ላይ የተገኙት የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ምርምር ለማንኛውም አገራዊ ልማት እና ዕድገት መሠረት መሆኑን ጠቅሰው፣ እንደ ተቋም ብሎም እንደ አገር ተፈላጊውን ለውጥ ለማስመዝገብ ጥናት እና ምርምር ፋይዳዉ የጎላ መሆኑን ጠቅሰዋል።

አፈ-ጉባኤው አክለውም፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ አውጪ እንደመሆኑ መጠን የሚያወጣቸው ሕግጋት፣ የሚወሰናቸው ውሳኔዎች እና አፈፃፀሞቹ በጥናት እና ምርምር ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑ እንደሚገባ በማንሳት፣ በዚህም መሠረት ጥናት እና ምርምሮች ለሕግ አውጪው አካል ሚናው የጎላ ነው ማለታቸው ተሰምቷል።

አስቀድሞ ሐምሌ ሦስት ቀን፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስቴር ዴኤታዋ ክብርት መሠረት ኃይሌ እና በተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ አማካኝነት የቀረበው ጽሑፍ፣ የሕዝብ ውክልና ሥራዎች አፈፃፀምን ለማላቅ ተጨማሪ ሥራዎች እንደሚያስፈልጉ ያመላከተ ነበር። ጥናቱ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 6ኛ ዙር የምርጫ ዘመን የተከናወኑ የሕዝብ ውክልና ሥራዎች አፈፃፀም ስኬቶች እና ተግዳሮቶችን በማጥናት የወደፊት አቅጣጫ ማመላከትን ዓላማ በማድረግ የተቃኘበት ነውም ተብሏል። በጥናቱ ማጠቃለያም፣ በ6ኛው ዙር የምርጫ ዘመን የሕዝብ ውክልና ሥራ ስኬቶች ከሆኑት ውስጥ ለተከታታይ አራት ዓመታት የውክልና ሥራ መሠራቱ፣ የምክር ቤት አባላት ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር ጠንካራ ትስስር እየፈጠሩ መምጣታቸው፣ የሕዝብ ጥያቄዎች ሳይንጠባጠቡ ለአሥፈፃሚ አካላት መድረሳቸው እና ሌሎችም በጥናቱ የተረጋገጡ የሕዝብ ውክልና ሥራዎች ውጤቶች መሆናቸው፣ በጹሑፍ አቅራቢዎቹ እንደራሴዎች ተጠቅሷል።

ሌላይኛው ጥናታዊ ጹሑፍ ርዕሰ-ጉዳይ፣ "ኢትዮጵያን ለዘመናት በማስተሳሰር ያሻገረ ሀገር በቀል ዕውቀትን እንዴት ከዘመናዊ ዲሞክራሲያዊ አሠራር ጋር ማገናኘት ይቻላል" በሚል፣ በዶ.ር. በዕውነቱ ኃይሉ የቀረበው ጥናት ነበር። ሀገር በቀል ዕውቀት ሲባል ከምዕራባውያኑ በተላቀቀ መንገድ ከማኅበረሰቡ የተማርነው፣ አብሮን ያደገ የኢትዮጵያዊነታችን ስሪት የሆነ ማለት እንደሆነ ያነሱት በዕውነቱ፣ በዚህም መሠረት ኢትዮጵያ እንደ አገር ለዘመናት ፀንታ የቆየችው በ'ራሷ ዕውቀት እና እውነት ውስጥ በመኖሯ ነው ብለዋል ተብሏል። ሀገር በቀል ዕውቀትን በዛሬዋ ኢትዮጵያ በተቋም ደረጃ በፓርላማ ውስጥ ይህንን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በመገንባት የላቀ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል በጥናታቸው ያነሱት ጹሑፍ አቅራቢው፣ ይህ ሀገር በቀል ዕውቀት በተለያዩ የአገሪቱ የማሻሻያ ፍኖተ ካርታዎች ውስጥ በተቃኙ የተለያዩ ንዑስ ክፍሎች ውስጥ ተካቶ ቢታይም፣ ይህ ሂደት ተጠናክሮ ተቋማዊ መልክን ባላበሰ ተግባር ከመከወን አኳያ ተጨማሪ ሥራዎች እንደሚያስፈልጉ አጥኚው ጠቁመዋል።



ጉባኤው በከፊል

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ለሀገር በቀል ኢኮኖሚ ትግበራ ውጤታማነት የጀመራቸውን ሥራዎች አጠናክሮ እንዲቀጥል የተጠቆመበት ደግሞ ሌላይኛው ጥናታዊ ጹሑፍ ነበር። ዳንኤል በየራ የተባሉ አጥኚ ባቀረቡት ይኸ ጹሑፍ፣ ለዐብይ ኢኮኖሚው ማሻሻያ ትግበራ ውጤታማነት፣ ምክር ቤቱ የተቋማትን የአቅም ክፍተቶች በመፈተሸ፣ ተጠያቂነትን በማስፈን እና የጥራት ማሻሻያዎች ላይ ያተኮረ ሥራ ሊሰራ እንደሚገባ አጽንዖት ተሰጥቶበታል ተብሏል። በብሔራዊ ምርጫ ቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ተስፋዬ ንዋይ አማካኝነት ደግሞ፣ በሕግ አወጣጥ፣ ሕግ ማመጨት እና የሕዝብ ተሳትፎን በተመለከተ ጥናታዊ ጽሑፍ ቀርቧል። አጥኚው በጽሑፋቸው፣ የተለያዩ አገራትን ተሞክሮ በማጣቀስ ምክረ-ሐሳብ ያቀረቡ ሲሆን፣ ምክር ቤቱ ከክልሎች ጋር በመናበብ ሥራ ሊሰራ እንደሚገባው እና ጠንካራ የቅድመ-ምርመራ ሥራዎች ላይም ማተኮር እንዳለበት ምክረ-ሐሳብ አቅርበዋል ተብሏል፡፡ በመጨረሻም፣ በጉባኤው መዝጊያ ላይ የተገኙት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ሎሚ በዶ፣ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች ወደ ተግባር ገብተው የሕዝቡን ችግር እንዲፈቱ ይደረጋል ሲሉ ተደምጠዋል። አፈ-ጉባኤዋ አክለውም፣ በጥናት እና በምርምር የተገኙ ምክረ-ሐሳቦችን መሠረት በማድረግ ተለዋዋጭ የሆኑ አገራዊ ጉዳች እንደሚፈቱ ጠቅሰው፣ ጥናቶቹ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ መናገራቸውን ከጉባኤው የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

# ሹመት

የወሩ የመጨረሻ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ክንውን፣ ሹመት መስጠት ነበር። አቶ አንድነት አድነውን፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በምክትል ዋና ጸሐፊ ማዕረግ የመንግስት ተጠሪ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ እንዲሆኑ እንደራሴዎቹ ሾመዋቸዋል።



አቶ አንድነት አድነው

# የብሪፅ ዳሰሳዊ ምልከታ

**በዐዋጅ ቁጥር 1394/2017 ዙሪያ**

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ ሐምሌ 10 ቀን 2017 ዓ.ም. ባካሄደው 2ኛ አስቸኳይ ስብሰባው፣ ነባሩን የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅ ቁጥር 1162/2011ን ለማሻሻል የቀረበለትን ረቂቅ ዐዋጅ መርምሮ በአብላጫ ድምጽ አፅድቋል፡፡ እንደ ምክር ቤቱ መረጃ ከሆነ፣ ዐዋጁን ማሻሻል ያስፈለገው በ2013 እና በ2014 ዓ.ም. የተካሄደውን ስድስተኛው አገር ዓቀፍ ምርጫን ተከትሎ የተስተዋሉ የሕግ ክፍተቶችን ለማሟላት መሆኑ ተገልጿል፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ አሥተዳደር ወደ ሥልጣን መምጣት በኋላ የተሻሻለው እና በሥራ ላይ የነበረው ሕግ የጸደቀው ጥቅምት 2012 ዓ.ም. ነበር። በዘጠኝ ክፍሎች እና በ 177 አንቀጾች የተዋቀረው አዲሱ ማሻሻያ፣ ምርጫን እንዲኹም የፓርቲዎችን ምዝገባ እና እንቅስቃሴ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሰፋ ያሉ ለውጦችን አድርጓል። ከዚኽ አንፃርም፣ 26 የዐዋጅ ድንጋጌዎች ላይ ማሻሻያ አድርጓል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ላለፉት ስድሰት ዓመታት ሥራ ላይ ያዋለውን ይኽንኑ ዐዋጅ አስመልክቶም፣ ለመገናኛ ብዙኃን ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቶ ነበር። መግለጫውን የሰጡት የቦርዱ ዋና ሠብሣቢ ሜላትወርቅ ኃይሉ፣ ቦርዱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ሰፊ ውይይት እና ምክክር ሲያደርግ ከቆየ በኋላ፣ 26 የዐዋጁ ድንጋጌዎች ላይ ማሻሻያ ማድረጉን አስታውቀዋል። በአገሪቱ ከ50 ሺሕ በላይ የምርጫ ክልል ጣቢያዎች መኖራቸውን የገለጹት ዋና ሠብሣቢዋ፣ የምርጫ ክልል ኀላፊዎች እንደ ምርጫ ክልል ጣቢያዎች ብዛት እንዲወሰን መጽደቁን ተናግረዋል። የምርጫ ጣቢያው ኀላፊ በምርጫ ሂደት የሚመጡ ቅሬታዎችን በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ፈጣን እና ግልጽ የቅሬታ ውሳኔዎችን መስጠት ይችላልም ተብሏል። ስለ ምርጫ ሕግ እና አፈጻጸም የበቁ አሥፈጻሚዎች በኹሉም የምርጫ ክልሎች እንደሚመደቡም አንስተዋል።

የማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁን መግለጫ ለእንደራሴዎቹ በንባብ ያቀረቡት አፈ ጉባዔው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ቦርዱ ሥልጣን እና ተግባሩን በተሻለ ዐቅም ለመፈጸም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የአሥተዳደር ሥራዎች ላይ ያሉ የሕግ ክፍተቶችን ለማስተካከል የቀድሞውን ዐዋጅ ማሻሻል አስፈልጓል ብለዋል፡፡ ማሻሻያ ዐዋጁን አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት እና የወሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት፣ በምክር ቤቱ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ እውነቱ አለነ በበኩላቸው፣ የማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁ በነባሩ ዐዋጅ ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶችን በማረም በፖለቲካ ፓርቲዎች አሥተዳደር፣ በምርጫ እና በምርጫ ሥነ-ምግባር የባለድርሻ አካላት መብት እና ግዴታ ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ድንጋጌዎችን ያካተተ መሆኑን ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል።

## የዐዋጁ ዋንኛ ድንጋጌዎች

ቀጣዩን የ2018ቱን ፌደራላዊ ምርጫ የተሻለ ርዕታዊ ሂደት እንዲኖረው ያደርጋል የተባለው የማሻሻያ ዐዋጁ፣ ሃያ ስድስት ድንጋጌዎች ላይ ማሻሻያ ሲያደርግ፣ ካሻሻላቸው እና ካካተታቸው ድንጋጌዎች መካከል ዋንኞቹ የሚከተሉት ናቸው፤

- አንድ ፓርቲ አገራዊ ፓርቲ ኾኖ ለመቋቋም፣ በሚኖርበት ክልል ከ 40 በመቶ የማይበልጥ መደበኛ ነዋሪዎች በአባልነት ሊኖሩት እንደሚገባ በዐዋጁ ተሻሽሎ መቅረቡ ተገልጿል። ከዚኽ ባለፈም፣ አገራዊ ነኝ የሚል ፓርቲ በአገሪቱ ካሉት ክልሎች ውስጥ፣ 50 በመቶ የሚኾኑ አካባቢዎች ላይ ተሳታፊዎች ሊኖሩት ይገባል ተብሎ ተደንግጓል።

- የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምርጫን አስመልክቶም ዐዲስ የተሰኘ ድንጋጌን ማሻሻያ ዐዋጁ ይዞ መጥቷል። ቀደም ሲል በክልል ምክር ቤቶች ብቻ ይደረግ የነበረው የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት ምርጫ፣ በዐዲሱ ዐዋጅ ከክልል ምርጫ ጋር ተደምሮ በሕዝብ ቀጥተኛ ምርጫ እንዲካሄድ ተደንግጓል።

- በማሻሻያው መሰረት የአግባብ ጥሰት መፈፀሙ የተረጋገጠ የፖለቲካ ፓርቲን ቦርዱ ከምዝገባ ከመሰረዙ በፊት የጥሰቱን አይነት፣ ክብደት እና ሌሎች ኹኔታዎችን ከግምት በማስገባት የፖለቲካ ፓርቲውን ከመሰረዙ በፊት ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ታግዶ እንዲቆይ ሊወሰን መቻሉም አንዱ የዐዲሱ ዐዋጅ ድንጋጌ ነው። የታገደ የፖለቲካ ፓርቲ እገዳው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜያት ከማንኛውንም አይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ፣ በየትኛውም ደረጃ በሚደረግ ምርጫ ላይ እንዲኹም በጋራ ምክር ቤት ውስጥ መሳተፍ ይከለከላል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ ከመንግሥት ከሚሰጥ ደጋፍ ተጠቃሚ እንደማይሆን ዐዋጁ ደንግጓል።

- የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት መዋጮን ከሠራተኞቻቸው ደመወዝ ላይ በቀጥታ እየቆረጡ አባል ወደ ሆኑበት የፖለቲካ ፓርቲ የባንክ ሒሳብ እንዳያስገቡ መከልከሉም አንዱ የማሻሻያው አንኳር ድንጋጌ ነው። ከዚኽ ባለፈም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዕጩዎች ከማናቸውም ሰው የሚሰጥን ስጦታ ወይም እርዳታን በግላቸው እንዳይቀበሉም ዐዋጁ ከልክሏል፤ ይኽንን ዓይነቱን ስጦታ ወይም እርዳታ መቀበል የሚችሉት በፓርቲው በኩል እንዲሆንም ማሻሻያው ደንግጓል። በዚኽ ዓይነት መልኩ እርዳታ የተቀበለ ዕጩ ድርጊቱ በተፈጸመ ወይም መፈጸሙን ባወቀ በ48 ሰዓት ውስጥ ለምርጫ ቦርዱ ማሳወቅ እና በዕጩነት ላቀረበው ፓርቲ የተደረገውን ስጦታ ወይም እርዳታ ማስረከብ እንዳለበትም በማሻሻያ ዐዋጁ ላይ ተቀምጧል።

- ማሻሻያው፣ በኹሉም አካባቢዎች በተመሳሳይ ጊዜ ጠቅላላ ምርጫ ማካሄድ በማይቻልበት ጊዜ ምርጫው በተለያየ ጊዜ ሊካሄድ እንደሚችልም ደንግጓል። ማሻሻያ ዐዋጁ፣ በተመሳሳይ ጊዜ ጠቅላላ ምርጫ ለማከናወን የማያስችሉ በሚል የዘረዘራቸው ጉዳዮች የፀጥታ ችግር፣ ወረርሽኝ፣ የተፈጥሮ አደጋን የመሰሉ ኹኔታዎችን ሲሆን፤ እነዚኽን ዓይነት ኹኔታዎች ሲያጋጥሙ ምርጫ ቦርድ ስለ ጉዳዩ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመመካከር ምርጫውን በተለያየ ጊዜ እንዲካሄድ ሊያደርግ እንደሚችል ሰፍሯል።

- ዐዲሱ ዐዋጅ፣ ዕጩዎች እና መራጮች ከተመዘገቡ በኋላ ስለሚራዘም ምርጫም አዲስ አሠራር አስፍሯል። በማሻሻያው መሠረት፣ ምዝገባ ከተደረገ በኋላ የተራዘመ ምርጫ በስድስት ወራት ውስጥ ካልተካሄደ፣ የዕጩዎች እና የመራጮች ምዝገባ በአዲስ መልክ ይካሄዳል ተብሏል። በተራዘመ ምርጫ የተመረጡ አሸናፊዎች የተወካይነት ቆይታም በሚቀላቀሉት ምክር ቤት ቀሪ የሥራ ዘመን እንደሚወሰን ዐዋጁ አስፍሯል። ከዚኽ ጭብጥ ባለፈም፣ አንድ ምክር ቤት የሥራ ዘመኑ ሊጠናቀቅ የቀረው ጊዜ አንድ ዓመት እና ከዚያ በታች ከሆነ፣ የተራዘመው ምርጫ አይካሄድም ሲል ምርጫ ቢራዘምም ሊካሄድ የማይችልበትን ኹኔታም ድንጋጌው አስቀምጧል።

- የመምረጥ የዕድሜ ገደብ ላይም ዐዋጁ ማሻሻያ አድርጓል። በማሻሻያው መሠረት፣ በምርጫው ዕለት 18 ዓመት የሚሞላቸው ዜጎች የመምረጥ፣ እንዲኹም 21 ዓመት የሚሞላቸው እጩዎች የመወዳደር መብትን አግኝተዋል።

- የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ግንባር እና ቅንጅቶች ከሚያቀርቧቸው ዕጩዎች መካከል ቢያንስ 20 በመቶውን ሴቶች እንዲያደርጉ የሚያስገድደው ክፍልም ዓይነተኛ የማሻሻያው ድንጋጌ ነው።

## የዐዋጁ ጠንካራ ጎኖች

- ከባለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲኽ፣ በአገር ደረጃ አዳዲስ ክልሎች ተመስርተው ፌዴሬሽኑን መቀላቀላቸው ይታወቃል። ከዚኽ አኳያም፣ የትኛውም በአገር ዓቀፍ ደረጃ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ እና በዚያው ልክ የፌደራል ምርጫው ውስጥ መሳተፍ የሚሻ የፖለቲካ ፓርቲ ቢያንስ በስድስት ክልሎች ውስጥ አባላት እንዲኖሩት የሚያስገድደው የዐዋጁ ማሻሻያ ክፍል ቀዳሚ በጎ ድንጋጌ ነው።

- በማሻሻያ ዐዋጁ፣ የመንግስት ሠራተኞች ምርጫ በሚወዳደሩበት ጊዜ ደመወዝ እየተከፈላቸው በምርጫ ይወዳደራሉ የሚለው ድንጋጌ ከዚኽ በፊት ያልነበረ ከመሆኑ አኳያ ብቻም ሳይሆን፣ ይኽ የማኅበረሰብ ክፍል፣ በምርጫ ፖለቲካው ውስጥ እንዲሳተፍ አበረታች ድንጋጌ መሆኑ አሌ አይባልምና አንዱ የማሻሻያው ጠንካራ ጎን ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው ነው።

- የሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ተሳትፎን አስመልክቶም፣ የተቀመጠው የማሻሻያ ድንጋጌ የዐዲሱ ዐዋጅ ጠንካራ ጎን ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች እጩ ሆነው ለመቅረብ ይጠበቅባቸው የነበረው ከፍተኛ የፊርማ መስፈርት፣ ከማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገደቦች በተጨማሪ የሥርዓት እንቅፋት ሆኖ መቆየቱ ግልጽ ነው። ዐዲሱ ዐዋጅ፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነት የሚያስፈልገውን የፊርማ ቁጥር ከ3,000 ወደ 1,500 በመቀነስ እንዲኹም በሌሎች የምርጫ ደረጃዎችም ተመሳሳይ ቅናሽ በማድረግ፣ ለፖለቲካዊ ተሳትፏቸው ጠንካራ ማበረታቻን መስጠቱ፣ ሌላይኛው የዚኹ ዐዋጅ ጠንካራ ድንጋጌ ነው።

- የምርጫ ሥራ ከፍተኛ ጊዜ እና ትጋት የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ቀደም ሲል የምርጫ አሥፈጻሚዎች ተሳትፎ ከማበረታቻዎች እጥረት የተነሳ ውስን ነበር። ዐዲሱ ዐዋጅ ለምርጫ ሥራ ለተሰማሩ የመንግሥት ሠራተኞች የሚከፈል ፈቃድ እንዲሰጥ በመደንገግ፣ ሙያዊ ብቃት ያላቸው እና ገለልተኛ የሆኑ ባለሙያዎች በምርጫ ሂደቱ ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያስችል ማበረታቻ የሚፈጥረበትን አውድ መፍጠሩም፣ ሊጠቀስ የሚችል የዐዋጁ ጠንካራ የድንጋጌው ክፍል ነው።

- የቴክኖሎጂ እና የመታወቂያ አጠቃቀምን የተመለከተው የዐዋጁ ክፍልም ሳይነሳ የማይታለፍ በጎ ገጹ ነው። ከአካታችነቱ አኳያም፣ ማየት እና መስማት የተሳናቸው ወገኖች፣ የዜግነት መብቶቻቸውን በቅጡ እንዲተገብሩት ያስችላልና፣ በጠንካራ ድንጋጌነቱ ሊነሳ የሚገባው ነው።

- ቀደም ሲል በክልል ምክር ቤቶች ብቻ ይደረግ የነበረው የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት ምርጫ፣ በዐዲሱ ዐዋጅ ከክልል ምርጫ ጋር ተደምሮ በሕዝብ ቀጥተኛ ምርጫ እንዲካሄድ ተወስኗል። ይህ ውሳኔ የፌዴራሊዝም ሥርዓቱን ከውክልና አሥተዳደር ወደ ይበልጥ ቀጥተኛ የሕዝብ ተሳትፎ የሚያሳድግ ሲሆን፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ ከዚኽ ቀደም ይነሱበት የነበሩትን ትችቶች ከማለዘቡ ባለፈ፣ የምክር ቤቱን ሕገ-መንግሥታዊነት እና ተጠያቂነት ከማጠናከሩ አኳያ፣ በጎ ሊባል የሚችለው የማሻሻያ ዐዋጁ ድንጋጌ ነው።

- የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የተመለከተው ድንጋጌም ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይሆንም። ከዚኽ ቀደም በግጭት እና አለመረጋጋት ሳቢያ ከመኖሪያ ቀያቸው ለተፈናቀሉ ዜጎች የፖለቲካዊ መብታቸውን በግልጽ የሚያረጋግጥ አሰራር አልነበረም። አኹን ግን፣ ዐዲሱ ዐዋጅ ተፈናቃዮች ከትውልድ የምርጫ ክልላቸው ትክክለኛ ሰነድ ካላቸው ድምጽ መስጠት እንደሚችሉ መደንገጉ፣ ቢያስን በቀጣዩ የ2018ቱ ምርጫ በተለያዩ አካባቢዎች ተፈናቅለው የሚገኙ ዜጎች ድምፃቸውን ማሰማት እንዲችሉ ያደርጋልና፣ የዐዋጁ አንድ ጠንካራ ጎን ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው ነው።

## የብሪጅ ምክረ ሐሳቦች

እነዚህ ሰፊ ማሻሻያዎች፣ በቀጣዩ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምኅዳር ላይ በጎ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል ተብሎ ይታሰባል። ይኹን እንጂ ለውጦቹ በተሳካ ኹኔታ ተግባራዊ እንዲሆኑ፣ ብሪጅ የሚከተሉትን ፖሊሲ ተኮር ነጥቦች በምክረ ሐሳብነት ማቅረብ ትሻለች።

- የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድን ተቋማዊ ነፃነት እና አቅም ማጠናከር፦ ይኽን መሰሎቹን በጎ የተባሉ ማሻሻያዎች ወደ መሬት ለማውረድ፣ ዓይነተኛ ሚና የሚኖረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መሆኑ ይታወቃል። ከዚኽ አኳያም፣ የምርጫ ቦርድ ገለልተኝነት መለካት ያለበት ከሕጋዊነት አኳያ ብቻም ሳይሆን ከበጀት እና ከአፈጻጸም ተቋማዊ ነፃነት አንፃርም መሆኑ ግልጽ ነው። ቦርዱ የዲጂታል የምርጫ ሥርዓትን ጨምሮ አዳዲስ ሂደቶችን ለማስፈጸም የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል እና የቴክኒክ አቅም እንዲያገኝ ድጋፍ ማድረግ ወሳኝ ነውና፣ በእነዚኽ ጭብጦች ላይ የፌደራል መንግሥቱም ሆነ የሚመለከታቸው የትኞቹም ተቋማት፣ ቦርዱን ለማጠናከር ከእነዚኽ ጉዳዮች አኳያ የየራሳቸውን ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርጉ ብሪጅ ማሳሰብ ትሻለች።

- የተአማኒነት ጉዳይ፦የምርጫ ተአማኒነት በምርጫ ቦርድ ብቻ የሚረጋገጥ አለመሆኑ ይታወቃል። ከምርጫ አጋሮች (የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሚዲያ፣ የሲቪክ ማኅበራት እና የፍትሕ አካላት) ጋር በጋራ የሲቪክ እና የምርጫ ትምህርቶችን ማካሄድ፣ የምርጫ ሂደትን በገለልተኝነት መታዘብ እና የሕግ የበላይነት እንዲከበር የጋራ አቋም መፍጠር ያስፈልጋል። ይኽ ሰፊ የትብብር ማዕቀፍ እንዲኖርም፣ የፌደራል መንግሥቱም ሆነ የየክልሎቹ መንግስታት፣ ቀጣዩ ምርጫ ሳይቃረብ በፊት ይኽ የትብብር ማዕቀፍ እንዲኖር በርትተው መስራት እንዳለባቸው ብሪጅ ማስታወስ ትሻለች።

- በቀደመው ስድስተኛው ፌደራላዊ ምርጫ የታዩትን የሎጂስቲክስ እና ፖለቲካዊ ተግዳሮቶች እንዳይደገሙ ለመከላከል፣ ኹሉም ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የጋራ አቋም እና አቅጣጫ ማበጀት፣ በተለይም ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና ከፌደራል መንግሥቱ ይጠበቃል እንላለን። ለዚኽ እንዲበጅም፣ ባለፉት ልምዶች ላይ ጥልቅ ትንተና በማካሄድ፣ ከትንተናው የሚቀሰሙትን ትምህርቶች ወደ ፖሊሲ እና ተቋማዊ አሠራር በመቀየር፣ ሰባተኛው አገራዊ ምርጫ ከቀደመው የተሻለ እንዲሆን በተለይም ምርጫ የማይካሄድባቸው አካባቢዎች እንዳይኖሩ ለማድረግ አስቸኳይ ቅድመ-ምርጫ ክንውኖች ይተገበሩ ዘንድ ብሪጅ ምክረ ሐሳቧን ታቀርባለች።

- የሴት አካል ጉዳተኛ ዕጩዎች፣ ማሰባሰብ የሚጠበቅባቸው የድጋፍ ፊርማ ከ2,000 ወደ 1,500 ዝቅ መደረጉ አዎንታዊ ቢሆንም ቅሉ፣ የወንድ አካል ጉዳተኛ ዕጩዎች በግልጽ አለመቀመጡ የዐዋጁ ጉድለት ይመስለናል፤ ይኽ ክፍተትም በዕጩ ምዝገባ ወቅቶች አላስፈላጊ ውዝግቦችን እንዳይፈጥር ያሰጋልና በተለይም የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከምርጫው ቀደም ያሉ መመሪያዎችን እና የአተገባበር ስልቶችን ይነድፍ ዘንድ ምክረ-ሐሳባችንን ማቅረብ እንሻለን።

- ምርጫን ፍትሓዊ እንዲሆን ከሚያደርጉት አውዶች ቀዳሚው ምቹ የምርጫ ከባቢ መፍጠር እንደሆነ ይታወቃል። ከዚኽ አንፃርም፣ የመወዳደሪያ ሜዳውን እኩል በማድረግ፣ ኹሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ዕጩዎች ያለ አንዳች ፍርሃት የፖለቲካ እንቅስቃሴያቸውን እንዲያካሂዱ ማረጋገጥ ወሳኝ ነው። ከዚኽ በተጨማሪም፣ ውጤታማ የግጭት አፈታት ስልቶችን በማስፈን፣ የመራጮችን እና የእጩዎችን ደኅንነት እና ነፃነት በማረጋገጥ፣ እንዲኹም ሰፊ የሲቪክ ምኅዳር እንዲኖር ቅድሚያ መስጠት ማስፈለጉም ግልጽ ነው። ይኽ አካሄድም፣ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ከማጠናከር ባሻገር የአገሪቱን ሰላም በማስጠበቁ በኩል ድርሻው አሌ አይባልምና፣ ዐዲሱ ዐዋጅ መሬት እንዲይዝ ኹሉም የምርጫው ተዋንያን የድርሻቸውን እንዲወጡ በዚኽ አጋጣሚ ብሪጅ ጥሪ ማድረግ ትፈልጋለች።

# መደምደሚያ

እነዚህ ማሻሻያዎች የኢትዮጵያን የምርጫ ማዕቀፍ ዘመናዊ እና ኹሉን አካታች ለማድረግ ወሳኝ እርምጃዎች ናቸው። ፍትሐዊ እና ነፃ ምርጫን ከማረጋገጥ ባሻገር፣ የሕዝብ ተሳትፎን ለማሳደግ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ተጠያቂነት ለማጎልበት እና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መሠረቶች ለማጠናከር ትልቅ አስተዋፅዖ አላቸው። ሰባተኛው አገር ዓቀፍ ምርጫ፣ እነዚኽ ማሻሻያዎች በተግባር የሚፈተኑበት ጊዜ እንደመሆኑ፣ አፈጻጸማቸውም የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሂደት በሆነ ልክ ያሻሻለዋል ተብሎ ይታመናል። ይኽንን ታሳቢ በማድረግ፣ የምርጫ ቦርድ በተወካዮች ምክር ቤት በፀደቀለት መመሥረቻ ዐዋጅ መሠረት፣ የገጠሙትን ፈተናዎች አልፎ ውስጣዊ ማሻሻያዎችን እያካሄደ እንደመሆኑ፣ ፍትሐዊ እና ተአማኒ ምርጫ እንዲካሄድ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል። ይኽ ማሻሻያ የምርጫ ሂደቱን ቀልጣፋ፣ ፍትሐዊ እና አስተማማኝ ለማድረግ ያለመ እንደመሆኑ፣ በዜጎች እና በፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፎ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በመድፈን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።

**እንደራሴ**

**እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።**

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**BRIDGE** Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.